# የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር

## የማዕድን ሥራዎች የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 271/2013

ሐምሌ 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ

በማዕድን ሥራ ባለፈቃድ ሊያዝ የሚችለዉ የፈቃድ ክልል ሥፋት ጣሪያ እንደ ማዕድኑ ተፈጥሮና አቀማመጥ እንዲሁም በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን መሠረት በማድረግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሕግና የአሠራር ክፍተቶችን በመድፈንና ለማዕድን ሥራዎች ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ዓለም አቀፍና ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሠማሩ ማመቻቸት እንዲሁም በቂ አቅም እና ዝግጅት ሳይኖራቸው በዘርፉ የሚሠማሩ ባለፈቃዶች የማዕድን ቦታን ያለአግባብ ይዘው እንዳይቀመጡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የማዕድንና የነዳጅ ሚኒስቴር በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (በአዋጅ ቁጥር 816/2006 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ (2) እንዲሁም በማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 423/2010 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የማዕድን ሥራዎች የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 271/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (በአዋጅ ቁጥር 816/2006 እንደተሻሻለው) ነው፤
2. "ደንብ" ማለት የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 423/2010 ነው፤
3. በአዋጁ እንዲሁም በደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
4. "በተለያዩ ቦታዎች የሚሰጥ ፈቃድ" ማለት አንዱ የፈቃድ ቦታ ከሌለኛው የፈቃድ ክልል ጋር ምንም የጋራ ድንበር የሌለው ወይም ኩታ ገጠም የሆነ ቦታ የሌላቸው መሬት ላይ የተሰጡ የተለያዩ ፈቃዶች ነው፤
5. "በአንድ ቦታ የሚሰጥ ፈቃድ" ማለት ለአንድ አይነት ማዕድን ወይም ለተለያዩ ማዕድናት ወይም በተፈጥሯቸው ተዋህደው (ተዛምደው) ለሚገኙ ማዕድናት በአንድ ፈቃድ ክልል ውስጥ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት RECORD Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት RECORD

5. የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት፡-

ሀ/ የጽንስ ክምችት ያለው የከበረ ብረት ነክ ማዕድናት ሲሆን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ 400 ካሬ ኪ.ሎ ሜትር ያልበለጠ፤

ለ/ የጽንስ ክምችት ያለው የከበሩና በከፊል የከበሩ ድንጋዮች ሲሆን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ 100 ካሬ ኪ.ሎ ሜትር ያልበለጠ፤

ሐ/ በደለል ለሚመረቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ10 ካሬ ኪ.ሎ ሜትር ያልበለጠ፤

5. <u>ይዞ መቆየት ፈቃድ</u>

ማንኛውም ይዞ መቆየት ፈቃድ የሚጠይቅ አመልካች በምርመራ ሥራ ውጤት በሚገኘው የክምችት መሠረት የአዋጪነት ጥናት አቅርቦ በአዋጁ ድንጋጌ መሠረት ፈቃዱን ለማግኘት ብቁ መሆኑ ከተረጋገጠ በዚህ መመሪያ ለማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የተፈቀደውን ክልል ስፋት ሊያገኝ ይችላል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>የማዕድን ማምረት ሥራ የፈቃድ ቦታ ስፋት ጣሪያ</u>

6. <u>የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ</u>

1. ማዕድኑ በባህሪው አንዱ ከሌላው ጋር ተቀላቅሎ ወይም ተዋህዶ (ተዛምዶ) የሚገኝ ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም አመልካች በአንድ ቦታ ላይ በአንድ ፈቃድ በአንድ ዓይነት ማዕድን የሚሰጥ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ሥራ ማምረት ፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ በደንቡ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት እንደ ሁኔታው በብሎክ የተከፋፈለ ሆኖ በሚከተሉት ንዑሳን አንቀጾች መሠረት መሆን አለበት።

2. የኮንስትራክሽን ማዕድናት፡-

ሀ/ የማጌጫ ድንጋይ (Dimension Stone) ሲሆን ከ 25 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

ለ/ እንደ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ገረጋንቲ ያሉ የግንባታ ማዕድናት ሲሆን ከ 20 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

6. "ጨው" ማለት ለምግብነትና ለኢንዱስትሪ ግብዓት ሊውል የሚችለውን ሶዲየም ክሎራይድ (NaCl) ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከማዕድን ቅኝት እና ከባሕላዊ ማዕድን ሥራ ፈቃዶች በስተቀር በሁሉም የማዕድን ሥራ ፈቃዶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የማዕድን ምርመራና ይዞ የመቆየት የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ

## 4. ማዕድን ምርመራ ፈቃድ

1. ማዕድኑ በባህሪው አንዱ ከሌላው ጋር ተቀላቅሎ ወይም ተዋህዶ (ተዛምዶ) የሚገኝ ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም አመልካች በአንድ ቦታ ላይ በአንድ ፈቃድ በአንድ ዓይነት ማዕድን የሚሰጥ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ በደንቡ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት እንደ ሁኔታው በብሎክ የተከፋፈለ ሆኖ በሚከተሉት ንዑሳን አንቀጾች መሠረት መሆን አለበት፡፡

2. ለኮንስትራክሽን ማዕድናት፡-

   ሀ/ የማጌጫ ድንጋይ (Dimension Stone) ሲሆን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ 25 ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

   ለ/ እንደ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ገረጋንቲ ያሉ የግንባታ ማዕድናት ሲሆን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ 20 ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

3. ለኢንዱስትሪ ማዕድናት፡-

   ሀ/ ከፖታሽ እና ጨው ማዕድን በስተቀር ማንኛውም የኢንዱስትሪ ማዕድን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ 200 ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

   ለ/ የፖታሽ ማዕድን ሲሆን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ 500 ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

   ሐ/ በጠጣር መልክ የሚገኝ የጨው ማዕድን ሲሆን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ 100 ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

   መ/ በውኃ አካላት ላይ ያለ ማዕድን ሲሆን በተጠየቀው ማዕድን ዓይነት የብቻ የሆነ መብት የሚያሰጥ ሆኖ የፈቃድ ክልል ስፋቱ የውኃው አካል ሙሉ በሙሉ ይሆናል፡፡

4. የብረት ነክ ማዕድናት ሲሆን የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከ 300 ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር

2. የኮንስትራክሽን ማዕድናት:-

ሀ/ የማጋጌጫ ድንጋይ (Dimension Stone) ሲሆን ከ 40 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

ለ/ እንደ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ገረጋንቲ ያሉ የግንባታ ማዕድናት ሲሆን ከ 30 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

3. የኢንዱስትሪ ማዕድናት:-

ሀ/ ማዕድኑን እንደ ሲሚንቶ ወይም ሴራሚክ ኢንደስትሪዎች በግብዓትነት ለራሱ ፋብሪካ ለሚጠቀም አመልካች ሲሆን ከ 75 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

ለ/ አመልካቹ ያመረተውን ማዕድን አሽጎ፣ አቀነባብሮ ወይም ዕሴት ጨምሮ ለገበያ የሚያቀርበው ሲሆን ከ 50 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

ሐ/ አመልካቹ ያመረተውን ማዕድኑን በጥሬ ለገበያ የሚያቀርበው ሲሆን ከ 40 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

መ/ በውኃ አካል ላይ ያሉ ማዕድናት ሲሆን የባለፈቃዱ ዓመታዊ የማምረት አቅም እና በማዕድኑ ክምችት መጠን ተገናዝቦ የሚሰጥ ይሆናል:: ሆኖም ቀሪው የማዕድን ክምችት መጠን ተገናዝቦ የሚበልጠው ወይም የሚተርፈው ክምችት ለሌላ አመልካች የሚሰጥ ይሆናል::

4. ብረት ነክ ማዕድናት ሲሆን ከ 75 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

5. የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት:-

ሀ/ የጅንስ ክምችት ያለው የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን ከ 75 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

ለ/ በደለል ለሚመረቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን ከ 40 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት RECORD Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት RECORD Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry

3. በኢንዱስትሪ ማዕድናት፡-

ሀ/ ማዕድኑን እንደ ሲሚንቶ ወይም ሴራሚክ ኢንደስትሪዎች በግብዓትነት ለራሱ ፋብሪካ ለሚጠቀም አመልካች ሲሆን ከ 75 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

ለ/ አመልካቹ ያመረተውን ማዕድን አሽጎ፣ አቀነባብሮ ወይም ዕሴት ጨምሮ ለገበያ የሚያቀርበው ሲሆን ከ 30 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

ሐ/ አመልካቹ ያመረተውን ማዕድኑን በጥሬ ለገበያ የሚያቀርበው ሲሆን ከ 20 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

መ/ በውኃ አካል ላይ ያሉ ማዕድናት ሲሆን የባለፈቃዱ ዓመታዊ የማምረት አቅም እና በማዕድኑ ክምችት መጠን ተገናዝቦ የሚሰጥ ይሆናል። ሆኖም ቀሪው የማዕድን ክምችት መጠን ተገናዝቦ የሚበልጠው ወይም የሚተርፈው ክምችት ለሌላ አመልካች የሚሰጥ ይሆናል።

4. ብረት ነክ ማዕድናት ሲሆን ከ 50 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

5. የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት፡-

ሀ/ የጽንስ ክምችት ያለው የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን ከ 50 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

ለ/ በደለል ለሚመረቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን ከ 30 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚመረት ሆኖ ትክክለኛው የቦታ ስፋት በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ በተገኘው ክምችት መጠን ይሆናል፤

7. <u>የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ</u>

1. ማዕድኑ በባህሪው አንዱ ከሌላው ጋር ተቀላቅሎ ወይም ተዋህዶ (ተዛምዶ) የሚገኝ ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም አመልካች በአንድ ቦታ ላይ በአንድ ፈቃድ በአንድ ዓይነት ማዕድን የሚሰጥ የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ሥራ ማምረት ፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ በደንቡ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት እንደ ሁኔታው በብሎክ የተከፋፈለ ሆኖ በሚከተሉት ንዑሳን አንቀጾች መሠረት መሆን አለበት።

8. <u>ስለልዩ አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ስለሚጨመር የፈቃድ ክልል</u>

የልዩ አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ቀደም ሲል በተሰጠው የባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ቦታ ላይ የተሻለ የማምረት ሥራ መሥራቱ ከተረጋገጠ ለአንድ ፈቃድ ከ 2,500 ካሬ ሜትር ያልበለጠ ስፋት ያለው ተጨማሪ መሬት ሊሰጠው ይችላል። ሆኖም ከአንድ ፈቃድ በላይ ሲሆን የሚሰጠው ተጨማሪ መሬት ጠቅላላ ስፋት ከ 5,000 ካሬ ሜትር መብለጥ የለበትም።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

9. <u>በተለያየ ማዕድን፣ በአንድ ማዕድን ወይም በተለያየ ቦታ የሚሰጥ የፈቃድ ብዛት</u>

ተጨማሪ የማዕድን ፈቃድ እንዲሰጠው የሚያመለክት ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱ ሊሰጠው የሚችለው ከዚህ ቀደም የነበረው የሥራ አፈጻጸም፣ የገንዘብ እና የቴክኒክ አቅም እንዲሁም በፈቃድ ማመልከቻ መወሰኛ መመመሪያ መሠረት በተዘረዘሩት መሥፈርቶች መሠረት ይሆናል።

10. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ክልል ስፋት ፈቃዱ እስኪታደስ ድረስ የነበረውን የቦታ ስፋት ይዞ የሚቀጥል ይሆናል። ሆኖም ፈቃዱ ሲታደስ የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያው በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ተስተካክሎ ሥራ ላይ መዋል አለበት።

11. <u>የተሻረ መመሪያ</u>

1. የፈቃድ ክልሎችን ጣሪያ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/1988 (ከነማሻሻያው) በዚህ መመሪያ ተሽሯል።
2. ማንኛውም የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

12. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)**
**የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር**
**ሚኒስትር**

መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum